የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ
# FEDERAL NEGARIT GAZETA
OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ዘጠነኛ ዓመት ቁጥር ፲፩
አዲስ አበባ—ኅዳር ፳፬ ቀን ፲፱፻፺፭

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

9th Year No. 11
ADDIS ABABA–3rd December, 2002

## ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፱/፲፱፻፺፭ ዓ.ም
የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ .................. ገጽ ፲፱፻፶፩

## CONTENTS

Proclamation No. 299/2002
Environmental Impact Assessment
Proclamation .......................................... Page 1951

### አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፱/፲፱፻፺፭
### የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ
### አዋጅ

የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ፣ የልማት ሃሣብ ንድፍ ሲዘጋጅ ቦታው ሲመረጥ፣ ሲገነባ ወይም ሲተገበር እንደዚሁም በመተግበር ላይ ያለ እንቅስቃሴ ሲሻሻል ወይም ሲቋረጥ የሚያስከትለውን ተፅዕኖ በመተንበይና አስቀድሞ በማረም በውል የታሰበበትን ልማት ለማምጣት የሚያግዝ በመሆኑ፣

መንግሥታዊ ሰነድ በአካባቢ ላይ ሊያስከትለው የሚችለውን ተፅዕኖ ለመለየት ገና ከመፅደቁ በፊት መገምገም፣ የመፅደቂያው ውሳኔ በሚሰጥበት ወቅት አካባቢያዊ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ባህላዊና ማህበራዊ ታሳቢዎችንና ግቦችን ዘላቂ ልማትን ለማምጣት በሚያመች ሁኔታ እንዲዋሃዱና እንዲቀናጁ ለማድረግ የሚያስችል በመሆኑ፣

አሉታዊ የአካባቢ ተፅዕኖዎችን መተንበይ፣ የመፍትሔ እርምጃዎችን መውሰድና ማሕበራዊና ኢኮኖሚያዊ ጠቃሚነታቸውን ማዳበር በሕገ መንግሥት የተደነገጉትን የአካባቢ ደህንነት መብቶችንና ዓላማዎችን የመተግበርን ሂደት የሚያግዝ በመሆኑ፣

የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አስተዳደራዊ ግልፅነትና በኃላፊነት ተጠያቂነት እንዲኖር ለማድረግ፣ በአጠቃላይ ራሱንና አካባቢውን በሚመለከቱ የልማት እቅዶች አወጣጥና ውሳኔ አሰጣጥ ላይ ሕዝቡን፣ በተለይም ደግሞ ማሕበረሰቦችን ለማሳተፍ የሚረዳ በመሆኑ፣

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭/፩/ መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

### ክፍል አንድ

፩· አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አዋጅ ቁጥር ፪፻፺፱/፲፱፻፺፭" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

### PROCLAMATION NO. 299/2002
### ENVIRONMENTAL IMPACT
### ASSESSMENT PROLAMATION

WHEREAS, environmental impact assessment is used to predict and manage the evironmental effects which a proposed development activity as a result of its design sitting, construction, operation, or an ongoing one as a result of its modification or termination, entails and thus helps to bring about intended development;

WHEREAS, assessment of possible impacts on the environment prior to the approval of a public instrument provides an effective means of harmonizing and integrating environmental, economic, cultural and social considerations into a decision making process in a manner that promotes sustainable development,

WHEREAS, the implementation of the environmental rights and objectives enshrined in the Constitution would be fostered by the prediction and management of likely adverse environmental impacts, and the maximaization of their socio-economic benefits.

WHEREAS, environmental impact assessment serves to bring about administrative transparency and accountablity, as well as to involve the public and, in particular, communities in the planning of and decision taking on developments which may affect them and its environment;

NOW, THEREFORE, in accordance with Article 55(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

### PART ONE

1. *Short Title*
   This Proclamation may be cited as the "Environmental Impact Assessment Proclamtion No. 299/2002."

ያንዱ ዋጋ 3·40
Unit Price

ነጋሪት ጋዜጣ ፖ·ሣ·ቁ· ፹ሺ፩
Negarit G.P.O.Box 80,001

፪· <u>ትርጓሜ</u>

በዚህ አዋጅ ውስጥ፣

፩· "ባለሥልጣን" ማለት የአካባቢ ጥበቃ ባለሥልጣን ማለት ነው፤

፪· "አካባቢ" ማለት በመሬት፣ በከባቢ አየር ፣ በአየር ሁኔታ እና በአየር ንብረት፣ በውሃ፣ በህያዋን፣ በድምፅ፣ በሽታ፣ በጣእም፣ በማህበራዊ ጉዳዮች እና በስነ ውበት ሳይወሰን፣ በተፈጥሮአዊ ሁኔታቸው ወይም በሰው አማካኝነት ተሻሽለው ወይም ተለውጠው የሚገኙ ነገሮች በሙሉና ያሉበት ቦታ፣ እንዲሁም መጠናቸውን ወይም ሁኔታ ቸውን ወይም ደግሞ የሰው ወይም የሌሎች ሕያዋን በጎ ሁኔታን የሚነኩ ተስተጋብሮቶቻቸው ድምር ነው፤

፫· "የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ" ማለት አንድ ፕሮጀክት ወይም መንግሥታዊ ሠነድ ተግባራዊ ሲሆን የሚያስከት ለውን ገንቢም ሆነ አፍራሽ ውጤት በቅድሚያ ለይቶ የማወቂያና የመመዘኛ ዘዴ ነው፤

፬· "ተፅዕኖ" ማለት በአካባቢ ወይም በንዑሳን ክፍሎቹ ላይ በሚፈጠር ለውጥ ምክንያት ማንኛውም በሰው ጤና ወይም ደህንነት፣ በዕፅዋት፣ በእንስሳት፣ በአፈር፣ በአየር፣ በውሃ፣ በአየር ንብረት፣ በተፈጥሮአዊ ወይም በባህላዊ ቅርስ፣ በሌላ ቁሳዊ ቁም አካል፣ወይም በአጠቃላዩ ሲታይ በአካበቢያዊ፣ በማሕበራዊ፣ በኢኮኖሚያዊ ወይም በባሕላዊ ገፅታዎች ላይ የሚከሰት ተከታይ ለውጥ ነው፤

፭· "የፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት" ማለት እንደሁኔታው የኢንቨስትመንት፣ የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ ለመስጠት ወይም የንግድ ድርጅት ለመመዝገብ በሕግ ሥልጣን የተሰጠው ማንኛውም የመንግሥት አካል ነው፤

፮· "ሰው" ማለት የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፤

፯· "በካይ" ማለት ፈሳሽ፣ ጠጣር ወይም ጋዝ የሆነ፣ በቀጥታም ሆነ ቀጥተኛ ባልሆነ መንገድ፤

ሀ) ያረፈበትን የአካባቢ ክፍል ጥራት በመለወጥ ጠቀሜታ የመስጠት አቅሙን የሚያጓድል፣ ወይም

ለ) በሰው ጤና ወይም በሌሎች ሕያዋን ላይ ጉዳት የሚያደርስ ወይም ሊያደርስ የሚችል መርዝን፣በሽታን፣ ክርፋትን፣ ጨረርን፣ ድምፅን፣ ንዝረትን፣ ሙቀትን ወይም ሌላ ክስተትን የሚያመነጭ፣ ማንኛውም ነገር ነው፤

፰· "ፕሮጀክት" ማለት በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ በማንኛውም መመሪያ ውስጥ በተጠቀሰ ርዕስ የሚካተት ማንኛውም አዲስ የልማት እንቅስቃሴ፣ ወይም በነባር ድርጅት ላይ የሚደረግ ጉልህ መስፋፋት ወይም ለውጥ፣ ወይም ደግሞ ተቋርጦ የነበረ ሥራን መልሶ ለመጀመር የሚደረግ እንቅስቃሴ ነው፤

፱· "የፕሮጀክት ባለቤት" ማለት ፕሮጀክቱ በመንግሥት የተወጠነ ሲሆን የሚመለከተው የመንግሥት አካል፣ ወይም በግሉ ዘርፍ የተወጠነ ሲሆን ባለሀብት የሆነው ሰው ነው፤

፲· "መንግሥታዊ ሠነድ" ማለት ፖሊሲ፣ ስልት፣ መርሐ ግብር፣ ሕግ ወይም የዓለም አቀፍ ስምምነት ነው፤

፲፩· "ክልል" ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፵፯/፩/ የተመለከቱት የአገሪቱ ክፍሎች ማለት ሲሆን፣ ለዚህ አዋጅ አፈፃፀም የአዲስ አበባ እና የድሬዳዋ አስተዳደሮችንም ይጨምራል፤

፲፪· "የክልል የአካባቢ መ/ቤት" ማለት ለአካባቢና ለተፈጥሮ ሀብት ጥበቃ ወይም ቁጥጥር በክልሉ ኃላፊነት የተሰጠው ማንኛውም የክልል የመንግሥት አካል ነው።

2. *Definitions*

In this Proclamation:

1) "Authority" means the Environmental Protection Authority;

2) "Environment" means the totality of all materials whether in their natural state or modified or changed by human; their external spaces and the interactions which affect their quality or quanitity and the welfare of human or other lving beings, including but not restricted to, land atmosphere, whetehr and climate, water, living things, sound, odor, taste, social factors, and aesthetics;

3) "Environmental Impact Assessment" means the methodology of identifying and evaluating in advance any effect, be it positive or negative, which results from the implementation of a proposed project or public instrument;

4) "Impact" means any change to the environment or to its component that may affect human health or safety, flora, fauna, soil, air, water, climate, natural or cultural heritage, other physical structure, or in general, subsequenlty alter environmental, social, economic or cultural conditions;

5) "Licensing Agency" means any organ of government empowered by law to issue an ivestment permit or a trade or operating license or a work permit or to register a business orgnaization, as the case may be;

6) "Person" means any natural or juridical person;

7) "Pollutant" means any substance whether liquid, solid or gas which directly or indirectly:

   a) alters the quality of any part of the receiving environment so as to affect its beneficial use adversely, or

   b) produces toxic substances, diseases, objectionable odour, radioactivity, noise, vibration, heat, or any other phenomenon that is hazardous or potentially hazardous to human health or to other living things.

8) "Project" mans any new development activity under any category listed in any directive issued pursuant to this Proclamation, major expansion or alteration or any existing undertaking, or any resumption of work that had been discontinued;

9) "Proponent" means any organ of government if in the public sector or any person if in the private sector that initiates a project;

10) "Public instrument" means a policy, a strategy, a programme, a law or an international agreement;

11) "Region" means any of those parts of Ethiopia specified as Regions under Article 47(1) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and, for the purpose of this Proclamation, includes the Addis Ababa and Dire Dawa Administrations;.

12) "Regional Environmental Agency" means any regional government organ entrusted by that Region with a responsibility for the protection or regulation of the environment and natural resources.

## ክፍል ሁለት

### ፫· ጠቅላላ ድንጋጌዎች

፩· ማንም ሰው በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፭ በወጣ መመሪያ መሠረት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልገውን ማንኛውንም ፕሮጀክት፣ ከባለሥልጣኑ ወይም ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ይሁንታ ሳያገኝ ተግባራዊ ለማድረግ አይፈቀድለትም።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ /፩/ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ከሚያስፈልገው ማንኛውም ፕሮጀክት የሚከተለውን ተፅዕኖ ኢምንት ነው ብሎ ከገመተ የፕሮጀክቱን ባለቤት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲያካሂድ ላያስገድደው ይችላል።

፫· ማንኛውም ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት የኢንቨስት መንት፣ የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ ከመሥጠቱ በፊት ከባለሥልጣኑ ወይም ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ፕሮጀክቱ ተግባራዊ እንዲሆን ይሁንታ መስጠቱን ማረጋገጥ አለበት።

፬· የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ ተቀባይነት ማግኘቱና ከባለሥልጣኑ ወይም ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ይሁንታ መሰጠቱ የፕሮጀክቱን ባለቤት ጉዳት በማድረስ ከሚከተል ኃላፊነት ነፃ አያደርገውም።

፭· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፬) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ፣ ከተጠያቂነት ነፃ መሆን የሚቻለው ጉዳቱ በተጎጂው በራሱ ወይም ደግሞ የፕሮጀክቱ ባለቤት ኃላፊነት በሌለበት በሦስተኛ ወገን መድረሱ ሲረጋገጥ ብቻ ነው።

### ፬· የተፅዕኖ መወሰኛ ታሳቢዎች

፩· የፕሮጀክት ተፅዕኖ ከፕሮጀክቱ መጠን፣ ከመካሄጃ ሥፍራው፣ ከባህሪዩ፣ ከክልል ተሻጋሪነቱ፣ ከሌሎች ተፅዕ ኖዎች ወይም ክስተቶች ጋር ከሚኖረው ተዳማሪነት፣ ከቆይታው፣ ወደ ነበረበት ሁኔታ ለመመለስ ከመቻሉ ወይም ካለመቻሉ፣ እንደዚሁም ከሌላ ተዛማጅ ገጽታዎች አኳያ መገምገም አለበት።

፪· ጠቃሚና ጎጂ ውጤቶች ካሉት፣ ነገር ግን ጠቃሚ ጎኑ በትንሹ ብቻ ከሚያመዝን ወይም መብለጥ አለመብለጡ ከሚያወዛግብ አንድ ፕሮጀክት ሊከተል የሚችልን አሉታዊ ተፅዕኖ ሲወስን ባለሥልጣኑ ወይም የሚከተለው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ወደ ጥንቃቄ እርምጃ በማዘንበል ፕሮጀክቱ ጉልህ አሉታዊ ተፅዕኖ ሊያስከትል ይችላል በማለት መወሰን አለበት።

### ፭· የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ስለሚያስፈልጋቸው ፕሮጀክቶች

፩· በዚህ አዋጅ መሠረት በሚወጣ በማንኛውም መመሪያ ውስጥ በተጠቀሰ ርዕስ በሚካተት በማንኛውም ፕሮጀክት ሁሉ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ መካሄድ አለበት።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) የተጠቀሰው መመሪያ፣

ሀ) አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከትሉ ይሆናል ተብለው ስለማይታሰቡ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የማያስፈልጋቸውን ፕሮጀክቶች፣ እና

ለ) አሉታዊ ተፅዕኖ ያስከትሉ ይሆናል ተብለው ስለሚታሰቡ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚያስፈልጋቸውን ፕሮጀክቶች፣

ለይቶ ማመልከት አለበት።

### ፮· ክልል ተሻጋሪ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ

፩· አንድ የፕሮጀክት ባለቤት ክልል ተሻጋሪና ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል ፕሮጀክት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ ሲያካሂድ፣ ጉዳት ይደርስባቸው ይሆናል ተብለው የሚገመቱ በየትኛውም ክልል የሚገኙ ማሕበረሰቦችን ማሳተፍ አለበት።

## PART TWO

### 3. *General Provisions*

1) Without authorization from the Authority or from the relevant regional environmental agency, no person shall commence implementation of any project that requires environmental impact assessment as determined in a directive issued pursuant to Article 5 of this Proclamation.

2) Without prejudice to Sub Article (1) of this Article, when the Authority or the relevant regional environmental agency believes that the possible impacts of the project are insignificant, it may decide not to require the concerned proponetn to conduct an environmental impact assessment.

3) Any licensing agency shall, prior to issuing an investment permit or a trade or an operating license for any project, ensure that the Authority or the relevant regional environmental agency has authorized its implementation.

4) Approval of an environmental impact study report or the granting of authorization by the authority or the relevant regional environmental agency does not exonerate the proponent from liability for damage.

5) Without prejudice to Sub Article (4) of this Article, exemption from liability shall be granted only when it is verified that it is the victim himself or a third party for whom the proponent is not responsible that has caused the damage.

### 4. *Considerations to Determine Impact*

1) The impact of a project shall be assessed on the basis of the size, location, nature, cumulative effect with other concurrent impacts or phenomena, trans-regional effect, duration, reversibility or irreversibility or other related effects of the project.

2) The Authority or the relevant regional environmental agency shall err on the side of caution while determining the negative impact of a project having both beneficial and detrimental effects, but which, on balance,is only slightly or arguably beneficial, and thus determine that it is likely to entail a negative significant impact.

### 5. *Projects Requiring Environmental Impact Assessment*

1) Every project which falls in any category listed in any directive issued pursuant to this Proclamation shall be subject to environmental impact assessment.

2) Any directive provided under Sub Article 1 of this Article shall, among other things, determine categoris of:

(a) projects not likely to have negative impacts, and so do not require environmental impact assessment;

(b) Projects likely to have negative impacts and thus require environmental impact assessment.

### 6. Trans-Regional Impact Assessment

1) A proponent shall carry out the environmental impact assessment of a project that is likely to produce a trans-regional impact in consultation with the communities likely to be affected in any region.

፪· ክልል ተሻጋሪ ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል ፕሮጀክት በሚካሄድበት ክልል ውስጥ የሚገኝ የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት፣ የፕሮጀክቱን የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባ ለባለሥልጣኑ እንዲቀርብ ማድረግ አለበት።

፫· ባለሥልጣኑ ክልል ተሻጋሪ የአካባቢ ተፅዕኖ ሊያስከትል የሚችል ፕሮጀክት የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባን መመርመር ከመጀመሩ በፊት ጉዳት ይደርስባቸው ይሆናል የሚባሉት በየሚመለከተው ክልል የሚገኙት ማሕበረሰቦች አስተያየት ተጠይቆ የተካተተ መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

## ክፍል ሦስት

### ፯· የፕሮጀክት ባለቤት ግዴታዎች

፩· አንድ የፕሮጀክት ባለቤት የፕሮጀክቱን የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ አካሂዶ፣ የፕሮጀክቱን አሉታዊ ተፅዕ ኖዎች በቅድሚያ ለይቶና ተፅዕኖዎቹን የማስቀሪያ ወይም የመቋቋሚያ ዘዴን በጥናቱ ውስጥ አካትቶ ባለሥ ልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ተገቢነታቸውን ከወሰነባቸው ሠነዶች ጋር የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባውን ለባለሥልጣኑ ወይም ለሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ማቅረብ አለበት።

፪· በፕሮጀክቱ ላይ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የሚካሄደው፣ የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባም የሚዘጋጀው ባለሥ ልጣኑ በሚያወጣው ማንኛውም መመሪያ የተዘረዘሩ መስፈርቶችን በሚያሟሉ ባለሙያዎች መሆኑን የፕሮ ጀክት ባለቤቱ ማረጋገጥ አለበት።

፫· የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማን ለማካሄድና የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባን ለማዘጋጀት የሚያስፈልገውን ወጪ የፕሮ ጀክቱ ባለቤት መሸፈን አለበት።

፬· አንድ የፕሮጀክት ባለቤት ፕሮጀክቱን ሲተገብር በተሰጠው ፈቃድ ውስጥ የተዘረዘሩ ግዴታዎችን ማሟላት አለበት።

### ፰· የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ

፩· የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባ፣ ባለሥልጣኑ ወይም የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት የፕሮጀክቱን መካሄድ ወይም አለመካሄድ ተገቢነት፣ እንዲሁም ሲካሄድ ሊኖረው የሚገባውን ሁኔታ ለመወሰን የሚያስችለውን በቂ መረጃ የያዘ መሆን አለበት።

፪· የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ ቢያንስ የሚከተሉትን ዝርዝሮች የያዘ መሆን አለበትተነ፣

ሀ) የፕሮጀክቱን ባህሪ፣ በጥቅም ላይ የሚውለውን ቴክኖሎጂና አጠቃቀም፣

ለ) ፕሮጀክቱ ሲተገበር እንዲሁም ቋሚ ሥራው ሲከናወን ወደ አካባቢ የሚለቀቀውን የበካይ ይዘትና መጠን፣

ሐ) የሥራው እንቅስቃሴ የሚጠይቀውን የኃይል ፍጆታና ምንጭ፣

መ· ሊከተል ስለሚችል ክልሏ ተሻጋሪ የአካባቢ ተፅዕኖ መረጃ፣

ሠ) በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ይከተላሉ ተብለው የተተመኑ አዎንታዊ ወይም አሉታዊ ተፅዕኖዎች ባህሪያትና የሚቆዩበት ጊዜ፣

ረ) አሉታዊ ተፅዕኖን ለማስወገድ፣ ለመቀነስ ወይም ለማቃለል የታቀዱ እርምጃዎች፣

ሰ· የአካባቢ አያያዝ ችግርን ለማቃለል የተነደፉ እቅዶች፣ የአደጋ መከላከያ ዝግጁነት፣ እና

ሸ) ፕሮጀክቱ በሚተገበርበትና እንደዚሁም ቋሚ ሥራው በሚከናወንበት ወቅት የውስጥ የቁጥጥርና የክትትል ሥራዎች የሚካሄዱባቸውን መንገዶች።

፫· ባለሥልጣኑየአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባን ለማዘጋጀትና ዘገባውን ለመመርመር የሚረዱ ሃሳቦችን የሚዘረዝሩ ‥መሪያዎችን ማውጣት አለበት።



2) The regional environmental agency in the region where a project with likely trans-regional impact is being initiated shall ensure the submission of the environmental impact study report of the project to the Authority.

3) The Authority shall, prior to embarking on the evaluation of an environmental impact study report of a project with likely trans-regional impact, ensure that the communities likely to be affected in each region have been consulted and their views incorporated.

## PART THREE

### 7. *Duties of a Proponent*

1) A proponent shall undertake an environmental impact assessment, identify the likely adverse impacts of his project, incorporated the means of their prevention or containment, and submit to the Authority or the relevant regional environmental agency the environmental impact study report together with the documents determined as necessary by the Authority or the relevant regional environmental agency.

2) A proponent shall ensure that the environmental impact of his project is conducted and the environmental impact study report prepared by experts that meet the requirements specified under any directive issued by the Authority.

3) The cost of undertaking an environmental impact assessment and preparing an environmental impact study report shall be borne by the proponent.

4) When implementing his project, a proponent shall fulfill the terms and condition of authorization.

### 8. *Environmental Impact Study Report*

1) An environmental impact study report shall contain sufficient information to enable the Authority or the relevant regional environmental agency to determine whether and under what conditions the project shall proceed.

2) An environmental impact study report shall contain, as a minimum, a description of:

(a) the nature of the project, including the technology and processes to be used;

(b) the content and amount of pollutant that will be released during impelemtation as well as during operation;

(c) source and amount of energy required for operatioin;

(d) information on likely trans-regional impacts;

(e) characteristics and duration of all the estimated direct or indirect, positive or negative impacts.

(f) measures proposed to eliminate, minimize, or mitigate negative impacts;

(h) contingency plan in case of accident; and

(i) procedures of self auditing and monitoring during implementation and operation.

3) The Authority shall issue guidelines that determine the elements necessary to prepare as well as evaluate an environmental impact study report.

፱. <u>የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ ምርመራ</u>

፩. ምርመራ እንዲካሄድበት ለባለሥልጣኑ ወይም ለሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት በሚቀርብ የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባ፣ ማንም ሊረዳው በሚችል ቋንቋ በአጭሩ የተዘጋጀ የጥናቱን መግለጫ የያዘና እንደዚሁም የጥናቱ መረጃ መሟላትንና ትክክለኛነቱን የሚያመላክት፣ አጭር መግለጫ መያዝ አለበት።

፪. ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት በ፲፭ የሥራ ቀናት ውስጥ፣ የሕዝብ አስተያየትንና የባለሙያዎች አስተሳሰብን በማመዛዘን የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናቱን ዘገባ ከመረመረ በኋላ፣

ሀ) ጎጂ ተፅዕኖ የማያስከትል መሆኑን ካመነ ያለምንም ቅድመ ሁኔታ ፕሮጀክቱን ይቀበላል፣ እንዲተገበርም ይሁንታውን ይሰጣል፣

ለ) ጎጂ ተፅዕኖዎቹን ለማስቀረት ወይም በበቂ ሁኔታ ለመቋቋም የሚቻል መሆኑን ካመነ ለማስቀረት ወይም ወደ ኢምንትነት ለመቀነስ የሚያስፈልጉትን ቅድመ ሁኔታዎች ዘርዝሮ እንዲሟሉ በማዘዝ ፕሮጀክቱ እንዲተገበር ይሁንታ ይሰጣል፣ ወይም

ሐ) ፕሮጀክቱ ተግባራዊ በሚሆንበት ጊዜ በአካባቢ ላይ የሚከተለውን አሉታዊ ተፅዕኖ በአጥጋቢ ሁኔታ ለማስቀረት እንደማይቻል ካመነ ትግበራውን ይከለክላል።

፲. <u>የፀደቀ የአካባቢ ተፅዕኖ ጥናት ዘገባ ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ</u>

፩. እንዲተገበር ይሁንታ የተሰጠው የፕሮጀክት የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባ፣ ይኸው ይሁንታ ሲሰጥ አብሮ የተመለከተውን የጊዜ ገደብ ተከትሎ ካልተተገበረ ተቀባይነቱ ይቀራል።

፪. የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) ድንጋጌ አተገባበር ተገቢ አለመሆኑን ሊያስረዳ የሚፈልግ የፕሮጀክት ባለቤት እንደአግባቡ ለባለሥልጣኑ ወይም ለሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ማመልከት ይችላል።

፫. ልዩ ሁኔታ ካላስገደደው በስተቀር፣ ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት ማመልከቻውን ከተቀበለበት ዕለት ጀምሮ በሰላሣ ቀናት ውስጥ የዘገባው ተቀባይነት ፀንቶ የሚቆይበት ጊዜ እንዲራዘም፣ ወይም የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማው እንዲከለስ ወይም እንደገና እንዲካሄድ፣ መወሰን አለበት።

## <u>ክፍል አራት</u>

፲፩. <u>የአዲስ ሁኔታ መከሰት</u>

የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባ ከቀረበ በኋላ ከባድ እንድምታ ያለው ቀደም ሲል ያልተጤነ እውነታ ቢከሰት ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት እንድምታውን ለማጤን እንዲቻል የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማው እንደአስፈላጊነቱ እንዲከለስ ወይም እንደገና እንዲካሄድ ማዘዝ ይችላል።

፲፪. <u>የትግበራ ክትትል</u>

፩. የፕሮጀክቱ ባለቤት፣ ፕሮጀክቱን በመተግበር ላይ የሚገኘው ለፕሮጀክቱ ትግበራ ይሁንታ በተሰጠበት ወቅት በገባው ቃል እና በተጣለበት ግዴታ ሁሉ መሠረት መሆኑን ለመገምገም ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት በፕሮጀክቱ አተገባበር ላይ ክትትል ማድረግ አለበት።

9. *Review of Environmental Impact Study Report*

1) An environmental impact study report that is submitted to the Authority or the relevant regional environmental agency for review shall include a brief statement summarizing the study in non-technical terms as well as indicating the completeness and accuracy of the information given in the study report.

2) The Authority or the relevant regional environmental agency shall, after evaluating an environmental impact study report by taking into account any public comments and expert opinions, within 15 working days:

(a) approve the project without conditions and issue authorization if it is convinced that the project will not cause negative impacts;

(b) approve the project and issue authorization with conditions that must be fulfilled in order to eliminate or reduce adverse limpacts or reduce adverse impacts to insignificance if it is convinced that the negative impacts can be effectively countered, or

(c) refuse implementation of the project if it is convinced that the negative impact cannot be stasifactoriey avoided

10. *Validity of Approved Environmental Impact Study Report*

1) The Authorization of an environmental impact study report shall expire if the project has not been implemented according to the time frame set during its authorization.

2) Any proponent who wishes to challenge the appropriateness of the provision of Sub Article (1) of this Article, to his project, may submit an application to that effect to the Authority or the relevant regional environmental agency, as may be appropriate.

3) Within 30 days from the receipt of an application pursuant to Sub Article (2) of this Article, the Authority or the relevant regional environmental agency shall,unless special circumstance so dictate, decide whether to extend the validity of the report or to order the revision or the redoing of the environmental impact assessment.

## PART FOUR

11. *Occurrence of New Circumstance*

If an unforeseen fact of serious implication is realized after the submission of an environmental impact study report, the Authority or the relevant regional environmental agency may, as may be appropriate, order the environmental impact assessment to be revised or to be redone in order to address the implication.

12. *Implementation Monitoring*

1) The Authority or the relevant regional environmental agency shall monitor the implementation of an authorized project in order to evaluate compliance with all commitments made by, and obligations imposed on the proponent during authorization.

፪. አንድ የፕሮጀክት ባለቤት እንዲተገብረው ይሁንታ የተሰጠውን ፕሮጀክት በገባው ቃል ወይም በተጣለበት ግዴታ መሠረት ካልተገበረ፣ ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት መወሰድ ያለበትን የእርምት እርምጃ በመግለጽ ማስጠንቀቂያ ሊሰጠው ይችላል።

፫. እንደአግባቡ ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ማንኛውንም ፕሮጀክት እንዲተገበር በዚህ አዋጅ አንቀጽ ፱(፪)ሀ ወይም (ለ) መሠረት የሰጠውን ይሁንታ ሲያግድ ወይም ሲሰርዝ ሌላ ማንም ፈቃድ ሰጪ መሥሪያ ቤት ለፕሮጀክቱ ትግበራ የሰጠውን ፈቃድ ይህንኑ ውሳኔ ተከትሎ ማገድ ወይም መሠረዝ አለበት።

፲፫. <u>የመንግሥት ሠነድ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ</u>

፩. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) መሠረት በወጣ በማንኛውም መመሪያ በሚገለጽ መደብ ውስጥ የሚካተት ማንኛውም የመንግሥት ሠነድ ከመፅደቁ በፊት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲካሄድበት መደረግ አለበት።

፪. በባህሪያቸው ቸል ሊባል የማይችል አካባቢያዊ ተፅዕኖ ያስከትሉ ይሆናል ተብለው የሚገመቱ የመንግሥት ሠነዶች መደብን ለመለየትና የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲካሄድባቸው ለማድረግ የሚያስችል መመሪያ ባለሥልጣኑ ማውጣት አለበት።

፫. በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፪) በወጣ በማንኛውም መመሪያ መሠረት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ በሚያስፈልገው መደብ የሚካተትን ማንኛውም የመንግሥት ሠነድ የሚያዘጋጅ የመንግሥት አካል በሠነዱ ላይ የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ የተካሄደበት መሆኑን ማረጋገጥ አለበት።

፬. ማንኛውም የመንግሥት አካል የሚያዘጋጀው ማናቸውም የመንግሥት ሠነድ ሊያስከትለው የሚችለው ተፅዕኖ እንዲገመገም ለማስቻል ከባለሥልጣኑ ጋር መተባበር አለበት።

፲፬. <u>የኃላፊነት ክፍፍል</u>

፩. ፈቃድ የመስጠቱ፣ የመተግበሩ ወይም የአተገባበር ቁጥጥሩ ድርሻ የፌዴራል መንግሥት አካል ከሆነ ወይም ፕሮጀክቱ ክልል ተሻጋሪ የአካባቢ ተፅዕኖ ያስከትል ይሆናል ተብሎ የሚታሰብ ከሆነ፣ የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባውን የመመርመር፣ ፕሮጀክቱ እንዲተገበር ይሁንታ የመስጠትና ክትትል የማካሄድ ኃላፊነት የባለሥልጣኑ ነው።

፪. ፈቃድ የመስጠቱ፣ የመተግበሩ ወይም የአተገባበር ቁጥጥር ድርሻ የክልል መንግሥት አካል ከሆነና ፕሮጀክቱ ክልል ተሻጋሪ የአካባቢ ተፅዕኖ ያስከትል ይሆናል ተብሎ የማይታሰብ ከሆነ፣ የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባውን የመመርመር፣ ፕሮጀክቱ እንዲተገበር ይሁንታ የመስጠትና አተገባበሩን የመከታተል ኃላፊነት የክልሉ የአካባቢ መሥሪያ ቤት ነው።

<u>ክፍል አምስት</u>

፲፭. <u>ስለሕዝብ ተሳትፎ</u>

፩. ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ማንኛውንም የአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባ ለሕዝብ ይፋ በማድረግ በዘገባው ላይ አስተያየት መጠየቅ አለበት።

፪. ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት በአጠቃላዩ የሕዝብ፣ በተለይም ደግሞ የፕሮጀክቱ አተገባበር ጉዳት ያስከትልባቸው ይሆናል ተብለው የሚገመቱ ማኅበረሰቦች አስተያየት፣ በአካባቢ ተፅዕኖ ጥናቱ ውስጥ መካተቱን፣ እንደዚሁም ምርመራው በሚካሄድበት ወቅት መጤኑን፣ ማረጋገጥ አለበት።

2) When the proponent fails to implement the authorized project in compliance with the commitments he entered into or obligations imposed upon him, the Authority or the relevant regional environmental agency may order him to undertake specified rectification measure.

3) Any other authorizing or licensing agency shall, in tandem with the Authority's or the relevant regional environmental agency's decision to suspend or cancel any authorization to implement a project, suspend or cancel the license it may have issued in favor of the project.

13. *Environmental Impact Assessment of public Instrument*

1) A public instrument included in any category in any directive issued pursuant to Sub Article (2) herein, shall, prior to approval, be subject to environmental impact assessment.

2) The Authority shall issue guidelines to determine the category as of public instruments which are likely to entail significant environmental impact and the procedure of their impact assessment.

3) Any organ or government which initiates a public instrument falling into any category which requires environmental impact assessment as determined in any directive issued pursuant to Sub Article (2) of this Article shall ensure that it has been subjected to environmental impact assessment.

4) Any government organ shall collaborate with the Authority to enable the evaluation of likely environmental impacts of any public instrument prepared by it.

14. *Jurisdiction*

1) The Authority shall be responsible for the evaluation of an environmental impact study report and the monitoring of its implementation when the project is subject to licensing, execution or supervision by a federal agency or when it is likely to produce trans—regional impact.

2) The regional environmental agency in each region shall be responsible for the evaluation and authorization or any environmental impact study report and the monitoring of its implementation if the project is not subject to licensing, execution and supervision by a federal agency and if it is unlikely to produce trans-regional impact.

PART FIVE

15. *Public participation*

1) The Authority or the relevant regional environemntal agency shall make any environmental impact study report accessible to the public and solicit comments on it.

2) The Authority or the relevant regional environmental agency shall ensure that the comments made by the public and in particular by the communities likely to be affected by the implementation of a project are incorporated into the environmental impact study report as well as in its evaluation.

፲፮· ስለማበረታቻ

፩· ባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት የተጎዳ አካባቢን መልሶ እንዲያገግም ለማስደረግ የተዘጋጀ ፕሮጀክት አተገባበርን አቅሙ በሚፈቅደው መሠረት ማገዝ አለበት።

፪· የዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) እንደተጠበቀ ሆኖ፣ የተጎዳ አካባቢን እንዲያገግም ለማድረግ ወይም ብክለትን ለማስቀረት ወይም የተበከለን ለማጽዳት ለተዘጋጀ ፕሮጀክት ባለሥልጣኑ አቅሙ በፈቀደ መጠን ተጨማሪ ወጪዎችን ለመሸፈኛ የገንዘብና የቴክኒክ ድጋፎች ማድረግ ይችላል።

፲፯· የቅሬታ አቀራረብ ሥርዓት

፩· ለፕሮጀክት ትግበራ በተሰጠ ይሁንታ ወይም በክትትል፤ ወይም ፕሮጀክቱን በሚመለከት ከባለሥልጣኑ ወይም ከክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት በተሰጠ በማንኛውም ሌላ ውሣኔ ላይ ቅር የተሰኘ ማንኛውም ሰው ቅሬታውን እንዳግባቡ ለባለሥልጣኑ ወይም ለሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ኃላፊ ማቅረብ ይችላል።

፪· በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (፩) በተደነገገው መሠረት፣ የባለሥልጣኑ ወይም የሚመለከተው የአካባቢ መሥሪያ ቤት የሥራ ኃላፊ ቅሬታው በደረሰው በሰላሣ ቀናት ውስጥ ውሣኔ መስጠት አለበት።

## ክፍል ስድስት

፲፰· ስለ ጥፋትና ቅጣት

፩· የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ድንጋጌዎች እንደተጠበቁ ሆኖ፣ ይህን አዋጅ ወይም ሌላ አግባብ ያለውን ሕግ ወይም መመሪያ የሚተላለፍ ማንኛውም ሰው ጥፋት ፈጽሞ አልና ቅጣት ይጣልበታል።

፪· ማንኛውም የፕሮጀክት ባለቤት የአካባቢ ተፅዕኖ ግምገማ እንዲካሄድበት የተደነገገበትን ማንኛውም ፕሮጀክት፣ ከባለሥልጣኑ ወይም ከሚመለከተው የክልል የአካባቢ መሥሪያ ቤት ይሁንታ ሳያገኝ ተግባራዊ ያደረገ እንደሆነ ወይም በአካባቢ ተፅዕኖ የጥናት ዘገባው ውስጥ ሀሰተኛ መግለጫ ያቀረበ እንደሆነ ጥፋት ፈጽሟልና ከሃምሣ ሺ ብር በማያንስና ከአንድ መቶ ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

፫· ማንኛውም ሰው በዚህ አዋጅ መሠረት ፈቃድ ሲሰጠው የተጣለበትን ግዴታ ካልተወጣ፣ ወይም ተፈላጊ ዝርዝሮችን በመዝገብ ሳያሰፍር ከቀረ ጥፋት ፈፅሞአልና ከአስር ሺ ብር በማያንስና ከሃያ ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

፬· በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው ድርጅት ጥፋት ሲፈጽም ድርጅቱ እንዲከፍለው ከተፈረደበት መቀጮ በተጨማሪ የሕጉን መከበር ለማረጋገጥ መፈጸም የሚገባውን ተግባር በትጋት ያልተወጣ በመሆኑ የሥራ መሪው ከአምስት ሺ ብር በማያንስና ከአሥር ሺ ብር በማይበልጥ የገንዘብ መቀጮ ይቀጣል።

፭· ይህን አዋጅ ወይም በሥሩ የሚወጣውን ማንኛውም ደንብ ወይም መመሪያ በመጣስ ጥፋተኛነቱ የተረጋገጠበትን ሰው፣ ከሚወሰንበት ከማንኛውም ቅጣት በተጨማሪ የደረሰውን ጉዳት በሙሉ በራሱ ወጪ እንዲያስተካክል ወይም እንዲተካ ፍርድ ቤቱ ማዘዝ ይችላል።

16. *Incentive*

1) The Authority or the relevant regional environmental agency shall, within the capacity available to it, support implementation of a project destined to rehabilitate a degraded environment.
2) Without prejudice to Sub Article (1) of this Article the Authority may, to the extent that its capacity allows, provide any environmental rehabilitation or pollution prevention or clean up project with financial and technical support to cover additional costs.

17. *Grievance Procedures*

1) Any person dissatisfied with the authorization or monitoring or any decision of the Authority or the relevant regional environmental agency regarding the project may submit a grievance notice to the head of the Authority or the relevant regional environmental agency, as may be appropriate.
2) The decision of the head of the Authority or relevant regional environmental agency shall, as provided under Sub Article (1) above, be issued within 30 days following the receipt of the grievance.

## PART SIX

18. *Offences and Penalties*

1) Without prejudice to the provisions of the Penal Code, any person who violates the provision of this Proclamation or of any other relevant law or directive commits an offence and shall be liable accordin-gly.
2) Any person who, without obtaining authorization from the Authority or the relevant regional environmental agency, or makes false presentations in an environmental impact assessment study report commits an offence and shall be liable to a in of not less than fifty thousand birr and not more than one hundred thousand Birr.
3) Any person commits an offence if he fails to keep records or to fulfill conditions of authorization issued pursuant to this Proclamation and shall be liable to a fine of not less than ten thousand Birr and not more than twenty thousand Birr.
4) When a juridical person commits an offence, in addition to whatever penalty it may be meted with, the manager who failed to exercise all due diligence shall be liable to a fine of not less than five thousand Birr and not more than ten thousand Birr.
5) The court before which a person is prosecuted for an offence under this Proclamation or regulations or directives emanating from it, may, in addition to any penalty it may impose, order the convicted person to restore or in any other way compensate for the damage inflicted.

## ክፍል ሰባት
## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

፲፱· ደንቦችን የማውጣት ሥልጣን

የሚኒስትሮች ምክር ቤት ይህን አዋጅ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ ደንቦችን ሊያወጣ ይችላል።

፳· መመሪያዎችን የማውጣት ሥልጣን

ባለሥልጣኑ ይህን አዋጅ በተሟላ ሁኔታ ተግባራዊ ለማድረግ አስፈላጊ የሆኑ መመሪያዎችን ሊያወጣ ይችላል።

፳፩· የመተባበር ግዴታ

ለዚህ አዋጅ አተገባበር ማንኛውም ሰው የመተባበር ግዴታ አለበት።

፳፪· ተፈጻሚነት የሌላቸው ሕጎች

ከዚህ አዋጅ ጋር ተቃራኒ የሆነ ሕግ ወይም አሠራር በዚህ አዋጅ ውስጥ በተመለከቱት ጉዳዮች ላይ ተፈጻሚነት አይኖረውም፤

፳፫· አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ ከኅዳር ፳፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም ጀምሮ የፀና ይሆናል።

አዲስ አበባ ኅዳር ፳፬ ቀን ፲፱፻፺፭ ዓ·ም

ግርማ ወልደጊዮርጊስ
የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
ፕሬዚዳንት

## PART SEVEN
## Miscellaneous Provisions

19. *Power to Issue regulations*

The Council of Ministers may issue Regulations necessary for the effective implementation of this Proclamation.

20. *Power to Issue Directives*

The Authority may issue directives necessary for the effective implementation of this Proclamation.

21. *Duty to Cooperate*

Any person shall have the duty to cooperate in the implemlentation of this Proclamation.

22. *Inapplicable Laws*

Any law or practice inconsistent with this Proclamation is inapplicable regarding matters provided herein.

23. *Effective Date*

This Proclamation shall come into force as of the 3rd day of December, 2002.

Done at Addis Ababa, this 3rd day of December, 2002.

GIRMA W/GIORGIS
PRESIDENT OF THE FEDERAL
DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ብርሃንና ሰላም ማተሚያ ድርጅት ታተመ
BERHANENA SELAM PRINTING ENTERPRISE